# ከጎርፍ በኋላ ውሃ ስለመጠጣት

## ከጎርፍ በኋላ መቼ እና እንዴት ውሃ በደህና መጠጣት እንደሚቻል የሚያስችል መረጃ

**Amharic | አማርኛ**

**OFFICIAL**

ከጎርፍ በኋላ የውሃ አቅራቢዎ የቧንቧ ውሃ ለመጠጥ ደህንነቱ የተጠበቀ ስለመሆኑ ምክር ይሰጥዎታል። የሚከተለውን ማሳሰቢያ ሊሰጡ ይችላሉ:-

**አትጠጡ የሚል ማሳሰቢያ**:- ውሃው ጎጂ ኬሚካሎች እና መርዞች አሉት እና መጠጣት በጣም ሊያሳምምዎ ይችላል።

**ውሃውን አፍሉ የሚል ማሳሰቢያ**:- ውሃው ጀርሞች ሊኖሩት ይችላል እና ከመጠቀምዎ በፊት ውሃውን ማፍላት አለብዎት። ያልፈላ ውሃ መጠጣት ለህመም ያጋልጣል።

### የቧንቧ ውሃ መጠጣት ካልቻሉ ምን ማድረግ እንዳለብዎት

የውሃ ባለስልጣን 'አትጠጡ የሚል ማሳሰቢያ' ካወጣ የቧንቧ ውሃ መጠጣት አይችሉም።

- ማድረግ ያለብዎት:-
  - ✓ ከተጎዳው አካባቢ የቧንቧ ውሃ አይጠጡ
  - ✓ አለማፍላት፣ ውሃው ላይ ክሎሪን ወይም ብሊች መጨመር ደህንነቱ የተጠበቀ አያደርገውም።
- የታሸገ ውሃ ለመጠጥ፣ ምግብ፣ መጠጦችን እና የሕፃን ፎርሙላ ለማዘጋጀት፣ በረዶ ለመሥራት፣ ጥርስ ለመቦረሽ ወይም እንደ ቤት እንስሳ የመጠጥ ውሃ ይጠቀሙ።
- በአንዳንድ ሁኔታዎች የቧንቧ ውሃውን የመጸዳጃ ቤቶችን ለማጠብ፣ እጅዎን ለመታጠብ፣ ገላዎን ለመታጠብ (ውሃው አለመጠጣትዎን ግን ያረጋግጡ) እና ልብሶችን ለማጠብ ሊጠቀሙበት ይችላሉ። ውሃውን መጠቀም ያቁሙ እና የቆዳ መቆጣት ወይም ሌላ ነገር ካጋጠምዎት ሐኪምዎን ያነጋግሩ።
- የውሃ አቅራቢዎ የቧንቧ ውሃ ለመጠጣት ደህንነቱ የተጠበቀ መሆኑን ያሳውቅዎታል።

### የቧንቧ ውሃ ማፍላት ከፈለጉ ምን ማድረግ አለብዎት

የውሃ አቅራቢዎ 'ውሃውን አፍሉ የሚል ማሳሰቢያ' ካወጣ የቧንቧ ውሃ ማፍላት ያስፈልግዎታል።

- ለመጠጥ አስተማማኝ እንዲሆን የቧንቧ ውሃዎን ለማፍላት:-
  - ✓ በቀጣይነት ብዙ አረፋ ከድስቱ ወይም ከማንቆርቆሪያው ስር እስኪያዩ ድረስ ውሃውን ያፍሉት።
  - ✓ ከመጠቀምዎ በፊት ውሃውን ያቀዝቅዙት።
  - ✓ በራስ የሚሰራ (አውቶማቲክ) ማጥፊያ ያላቸው ማንቆርቆሪያዎች ተስማሚ ናቸው። የተለያየ የሙቀት መጠን ባላቸው ማንቆርቆሪያዎች የሙቀቱን መጠን ውሃ በሚፈላበት ልክ መስተካከል አለባቸው።
  - ✓ የተፈላውን ውሃ በንጹህ እና ክዳን ባለው መያዣ ውስጥ ያከማቹ
  - ✓ ከመጠቀምዎ በፊት ውሃውን ያቀዝቅዙ
  - ✓ የመቃጠል ጉዳቶችን ለማስወገድ ጥንቃቄ መደረግ አለበት።
- የተፈላ ውሃ ፤ ለመጠጥ ፣ ለምግብ ዝግጅት፣ የሚጠጣ ነገር እንዲሁም ለህፃናት ፎርሙላ ለማዘጋጀት፤ በረዶ ለመስራት፣ ጥርስ ለመቦረሽ እና እንደ የቤት እንስሳ የመጠጥ ውሃ ጥቅም ላይ መዋል አለበት።
- ያልተፈላ ውሃ እጅን ለመታጠብ፣ ገላ ለመታጠብ መጠቀም ይችላሉ(ውሃውን አለመዋጥዎን ግን ያረጋግጡ)፣ መጸዳጃ ቤቶችን ለማጠብ፣ እቃ ማጠቢያ እና ልብስ ለማጠብ እና ለአትክልት ወይም ከቤት ውጭ ወለል ለማጠብ ሊያገለግል ይችላል።
- የውሃ አቅራቢዎ የቧንቧ ውሃው ሳይፈላ ለመጠጣት ደህንነቱ የተጠበቀ ሲሆን ያሳውቅዎታል።

### እርዳታ ያግኙ

- ከውሃ አቅራቢዎ መረጃ ለማግኘት በ <www.water.vic.gov.au/water-industry-and-customers/know-your-water-corporation> ያግኙት።
- የተበከለ ውሃ ጠጥቻለሁ ብለው ከሰጉ ወይም ተቅማጥ መሰል የበሽታ ምልክቶች ካጋጠሙዎት ሐኪምዎን ያነጋግሩ።

ይህን ህትመት በቀላሉ ሊያነቡት በሚችል መልኩ ለመቀበል፣ በ pph.communications@health.vic.gov.au ኢሜይል ያድርጉ